

**"ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ ፤የጻድቅ መታሰብያ ለዘላለም ይኖራል "**

*መዝሙር ፻፲፩፥፮*

# የአቡነ ተክለሃይማኖት አጭር ታሪክ

መታሰብያቸው ለዘላለም ከሚኖረው ቅዱሳን ውስጥ አንዱ ጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለሃይ ማኖት ናቸው ። ቅዱስ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቅዱስ ጸጋ ዘኣብና ቅድስት እግዚእሐርያ ከሚባሉ ቅዱሳን በሰሜን ሸዋ ሃገር ስብከት በቡልጋ አውራጃ ደብረጽላልሽ በተባለው ስፍራ መጋቢት ፳፬ ቀን በብሥራት መልአክ ተፀንሰው በ ፲፩፻፺፯ ዓ.ም ታህሳስ ፳፬ ቀን ተወለዱ። ጻድቁ አባ ታችን አቡነ ተክለሃይማኖት በእናታቸው መህጸን ሳሉ ልዑል እግዚአብሔር ስለመረጣቸው በተወለ ዱ በሶስት ቀናቸው በእናታቸው በቅድስት እግዚእሐርያ እቅፍ ሆነው አሃዱ አብ ቅዱስ አሃዱ ወል ድ ቅዱስ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው ለሥላሴ እንደ አባታቸው ቅዱስ ጸጋ ዘኣብ ምስጋና አቅርበዋ ል።

አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት በቀድሞው አጠራር ዞረሬ የአሁኑ የትኢሳ ሚካኤል ክርስትና ሲነሱ የክርስትና ስማቸው ፍስሐፅዮን ተባለ።እንደ ሕፃን በጥቂቱ ሲያድጉ ከቆዩ በኋላበሰባት ዓመታቸ ው ከቅዱስ ጸጋ ዘኣብ ትምህርት ጀምረው በስምንት ዓመታት ውስጥ ብሉይከሐዲስ ትርጓሜና ሥ ርዓተ ቤተ ክርስትያን አጠናቀቁ ።አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተወለዱ በ፲፭ ዓመታቸው በዘ መኑ ከነበሩት ግብጻዊ ጳጳስ አባጌርሎስ ዲቁና ማዕረግ ተቀብለውሲመለሱ የተለያዩ ተአምራት በጉዛ ቸው ላይ አሳይተዋል ። በተወለዱበት ደብር በዲቁናማዕረግ እያገለገሉ በቁመት በጥበብ እ የጎለመሱ ሲሄዱ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖትበተወለዱ በ ፳፪ ዓመታቸው ቅዱስ ጸጋ ዘኣብና እናታቸው ቅድስት እግዚእሐርያ በተከታታይወራቶች ውስጥ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩዋቸው።

" ሰው አለምን ቢገዛ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል። ነፍሱን ሊያድናት የወደደመስቀሌ ን ተሸክሞ ይከተለኝ " የሚለውን አምላካዊ ቃል አሰበው ከጓደኞቻቸው ጋር አራዊትሲያድኑ ከዛሬ ጀምሮ አራዊት ሳይሆን ሰዎች ታድናለህ ተብለው በታዘዙት መሰረት ከአባት ከእናታቸው ያገኙት ን ሃብት ንብረት በሙሉ ለነዳያንና ለቤተክርስትያን መጽውተው እንደሐዋርያ ለማስተማር ፥እንደ ሰማ ዕታት መከራ ለመቀበል ፥ እንደ መኖክሳት በሕርመት በጾምበጸሎት በብሕትውና ለመኖር ፥ቤታቸ ውን ክፍት ትተው የዳዊትን መዝሙር እየዘመሩ ሄዱ።



Created using easyPDF Printer
Click here to purchase a license to remove this image

ከዚያ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዲስ ሐዋርያ ዘኢትዮጵያ በሎ ሲሾማቸውስማቸውም ፍስ ሐፅዮን መባላቸው ቀርቶ ተክለ አብ ተክለ ወልድ ተክለ መንፈስ ቅዱስ ወይም ተክለሃይማኖት ተብለው እንዲጠሩ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል አዘዛቸው ።

ብፁወ ቅዱስ ፃድቁ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት የዘመድ ናፍቆትና የገንዘብ ፍቅር ጨርሶ ጠፋለትና የሚያስበውና የሚሰራው የእግዚአብሔርን ሕግ ብቻ ሆነ። ያለአንተ ጠባቅዬ ብወድቅ የሚያነሳኝ ብጠቃ የሚረዳኝ የለም እያለ ቁከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር ማስተማርና ድውያንን መ ፈወስ ጀመረ። ቤቱን ከፍቶ ጌታዬ ቤቴን ከፍቼ ትቼ ስለሄድኩኝ አንተም የመንግስተ ሰማያትን በር ክፈትልኝ ብሎ የሐዋርያትን ሥራ ወንጌልን ለማስተማር ቤቱን ጥሎትሄዷል። ትምህርቱና ተአምራቱ ሁሉ በየሀገሩ ደርሶ በእርሱ ስብከት ያመኑት ሰዎች ለእንጨት ለድንጋይ ከዚህም ሌላ ልዩ ልዩ ለሆኑ ጣኦታት የሚሰው አሉ ብለው ነገሩት ።በነርሱ መሪነት ሄዶ እንደነገሩት ሆኖ አገኘው ። ምን ምን ታመልካላችሁ ቢላቸው የምንሰግድለት የምናመልከው ዛፍ አለ አሉት። ስትሰግዱለት ምን ይላች ኋል ? አላቸው ። ከዛፍ ላይሆኖ ፈጣርያችሁ እኔ ነኝ ይለናል አሉ ።እኔም እንድሰግድለት ይዛችሁ ኝ ሂዱ አላቸው። ይዘውት ሲሄዱ ምንይዛችሁብኝ መጣችሁ ብሎ ጮኸባቸው ። ፈጣሪያችን የጠላህ ኋጢአተኛ ብትሆን ነው እሱ ኋጢአተኛውን ከሩቅ ያውቃልና ተመለሱ አይሆንም አሉት። ከዚያ ተመልሶበፈጠርከው ፍጥረት ሰይጣን ለምን ይጫወትበታል ? ብሎ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክትና አንቺ እንጨት ሰይጣን የሚያስትብሽ ዛፍ ተነቅለሽ ነዶ ብሎ ጠራት ። እረሷም ከነስሯ ተነቅላ ወደ እርሱ እየሮጠች መጣች። ወደ እርሱም ስትመጣ ከስሯ ያለው አፈርና ጠጠር እያወናጨፈች 24 ሰዎች ፈጀች።ያ እንጨቷ ላይ የነበረው ሰይጣን ወደየት ልሂድ? ብሎ ጮኸ።በል ቀድሞ እንዳሳት ካቸው በቃልህ አምላክ አለመሆንህን ግለጽና ውጣ ብሎ አዘዘው ። እርሱም ለቃሉ ታዞ ተናግሮ ወጥቶ ሄደ። እነዚያን አሳምኖ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ብሎ አጠመቃቸ ው። እንጨቷም የፈጀቻቸውን ሰዎችም አስነስቷል። ከዚህ በኋላ ቤተክርስትያን አሳንጾ የሚያስተምር ካህን መድቦላቸው እግዚአብሔር ወደ ጠራው ቦታ ሄዷል።

ቅዱስ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖትን ጌታችን መድኋኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያስተ ምሩ የጠራቸው በይፋት በአማራ ሳዶትና በሸዋ ክፍለ ሀገር ስለነበር ይህን ትዕዛዝ ከፈፀመ በኋላ የተ ጠራው ወደ ጉራጌ ነበር። እዚያም አስተምሮ አጥምቆ የአምላክን ፍቃድ እንደፈፀመ ለታላቅ ተጋድ ሎና አገልግሎት ወደ ወላሞ ሄደ። ከወላሞ ሀገር የነገሰው ሞተሎሚ የሚባለው ንጉስ ነበር። ሞተሎ ሚ የሚያመልከው በእግዚአብሔር ሳይሆን በጣኦት ነበር። ጻድቁአባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት ከዚያ እንደደረሰ ሞተሎሚ የሚያመልካቸውን ጣኦታት ስለሰበረ ንጉሱ ሳይሰማ አይገደለም ብለው አስረው ቀፈረ ውድም ለሚባለው ለንጉሱ ሹም አስረክበውታል።

አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት ከቀፈረውድም ቤት እንደገባ የሹሙ ልጅ ታሞ ስለነበርጋኔኑ ጮኸ አባታችንም ፀሎት አድርጎ ፈወሰው። ሌሎችንም ብዙ ድውያን በመፈወሱ ሹሙና ቤተሰቡ በአ ምላከ ተክለሃይማኖት አመኑና ተጠመቁ።

ጠብቅ ያሉትም ሰዎች ሹሙን አስረን የሰጠንህን ሰው ስጠንና ወደ ንጉሱ እንሂድ አሉት ። ሹሙ እኔ ሳልሞት እርሱን አልሰጣችሁም ብሎ ከለከላቸው። እነርሱም ሄደው ለሞተሎሚ ነገሩት ። ንጉሱም ተቆጥቶ ሁለቱም በስንሰለት ታስረው እንዲመጡ አዘዘ ። ይዘውት ቀረቡ በምን ምክን ያት ይሄን ሰው ወደእኔ እንድያመጡት ከለከልክ ቢለው ድውይ ሲፈውስ ጋኔን ሲያወጣ ስላየሁ አዎን ከልክያለሁ አለው ።አቡነ ተክለሃይማኖትንም ሀገርህ ወደየት ነው ?ከሀገህስ ወደዚህ ለምን መጣህ ? ቢለው ጣኦታትን ለማጥፋት ክርስትናን ለመስበክ መጥቻለሁ አለው። ጣኦታቱን አጥፍተህ አንተ ልትመለክ ነው? ብሎ ተናዶ ጦር ለመወርወር ቢቃጣጦሩ በእጁ ተጠምጥሞ ቀረ። በዚህ አይነት ጦመ ግራር ከሚባለው ታለቅ ገደል ቀፈረውድምና አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት እንዲጣሉ አዘዘና ሁለቱንም በቀፎ ውስጥ ገብተው በቆዳተለጉመው ቢጥሏቸው መልአክ እየተቀበለ አዳናቸው ቆፎውም እንደተለጎመ ይገኛል።

በዚህ አይነት እየተጣሉ የዳኑና ያመኑ ሁሉ ከእንጨትም ላይ ተሰቅሎ እንዲሞት ሰቀሉት ቢሰቀልም ለማሰር የወጣውን ሰው ዛፉ እንደአመለኛ ረግጦ ገደለው። እሱን ግን ውረድ እንደማለት አዘንብሎ ከምድር አሳረፈው። ገመዱም ከአንገቱ ወጥቷል ። በየጊዜው የሚደረገውን ታምራት

እያየ ሕዝቡ ሲያምን እርሱም እየተናደደ በሰይፍ ሲያስፈጅ ሰራዊቱተሚጦ ስላለቀ አንድ ሰው አጠቃለሁ ስትል ሰራዊትህ ጨርሶ አለቀ ጠላት ቢመጣብህ ማንንይዘህ ትዋጋለህ ? የሚል መካር ተነ ስቶ ስለመከረው ይልቅም ቀደም ብሎ በተክለሃይማኖትስብከት በመጀመርያ አምኖ የተጠመቀው ቀፈረውድም አማሃዶ በመሆን ረድቶት የማመንምልክት ያሳይ ጀመረ ። መንግስቴን እንዳይቀማኝ ነ ው እንጅ አምናለሁ ቢለው ስለዚህ እኔ

እፈፅመልሃለሁ ብሎ አቡነ ተክለሃይማኖትን አስጠርቶ አድነኝና በአምላክህ አምናለሁ አለው። በመጀ መርያ ሟርተኞቹን አድኑኝ በላቸውና ያድኑህ አለው። እነዚያን አድኑኝ ቢላቸው የአንዱን ስራይ አንዱ ሊያድነው ስለማይችል ማዳን አይቻለንም አሉት ። ከዚህ በኋላ አባታችን ሟርተኞች ሁሉ ተሰብስበው እንዲገጥሙት የሚያሸንፍ እርሱ የአምላክ ባለመዋል ነው ተብሎ በ40 ቀን ውስጥ ሟር ተኞ ተሰበሰቡ ። ሕዝቡ አንዳንድ ሸክም እንጨት አመጣ በቀጠሮው ቀን ነደደ ሟርተኞ ከእሳቱ ውስጥ ሁነው ይዘፍኑ ጀመር። ንጉሱን እንዳያምን መከሩት።በጨሻ ተክለሃይማኖት ከእሳቱ መሐል ገብቶ ደለዬ በመስቀል እሳቱን ባረከው ። ሟርተኞን በላቸው ቅዱስ አባታችን ግን ምንም ሳይነከው ከእሳቱ ውስጥ ወጣ። ሞተለሚ ከነሰራዊቱ አምኖ ተጠምቀዋል ። ንጉስ ሞተለሚ በሁሉም ነገር ሲያምን ትንሳኤ ሙታንን ግን በትምህርት አላምንም የማምነው ከዛሬ 25 አመት በፊት በዚሁ ስፍራ 13ሺህ ሰዎች በአንድቀን ሞተዋል ስጋቸው በስብሶ አጥንታቸው ፈርሷል ። እነሱን አስነስ ተህብታሳየኝ ትንሳኤሙታን መኖሩን አምናለሁ አለው። ቅዱስ አባታችንም ጸሎቱን ጨርሶ በዚህ በማልበረዴ አደባባይ ሙታችሁ የተቀበራችሁ ሙታን በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሕያዋን ሁናችሁ ውጡ ብሎ ጠራቸው። እነሱም ከመቃብር ወጡ ወዴት እንደነበሩ ጠየቃቸው። እነርሱም በሲኦል ውስጥ መቆየታቸውን ነገሩት። ሞተለሚ የተነሱትን ሙታን የነበሩበትን የስቃይቦታ ሰምቶ ሰ ቀጠጠው።ተንቀጠቀጠ ነፍሱ ትድን ዘንድ ብዙ ምጽዋት ሰጠ አብያተ ክርስትያናት አሳነጸ በምግባር በረታ።

ክቡር አባታችን በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ካህናት ዲያቆናት እየሾሙ በባሌ፥ በወላይታ፥ በሙገር፥በጉራጌ፥በሰላሌ ሀገሮች እተዘዋወሩ አሕዛብን በማጥመቅ ድውያንን በመፈወስ አብያተክር ስትያንን በማሳነጽ ለ12 አመታት አስተምረው አሁንም በጌታችን ፈቃድሥርዓተ አበው ለማድረስ ከአባበጸሎተ ሚካኤል ገዳም በሐይቅ እስጢፋኖስ ደብረዳሞ ገዳምበመሄድ በረድነት በትምህርት በ ቅዳሴ የተለመደውን ስራቸውን እየሰሩ ለ32 ዓመታት ከቆዩ በኋላ በደብረዳሞ ገዳም ከነበሩ ከአባ ዩ ሐኒ ገዳም ቡራኬ ተቀብለው ከገደሉ ሲወርዱ ሰይጣን ይወርዱበት የነበረውን ገመድ በመበጠሱ ስድ ስት ክንፍ ተሰጥቷቸው ገዳሙን ሶስት ጊዜዙረው ወደኢየሩሳሌምና ገዳማተ ግብጽን ለመጎብኘትና በ ዘመኑ ከነበሩትቅዱሳን በረከት ለመቀበል ሂደዋል።

ብፁወ ቅዱስ ፃድቁ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት ሐዋርያዊ ተልዕኮ ፈጽመው በእድሜ እ የገፉ ሲሄዱ የዘሩት ዘር እንክርዳድ እንዳያጠፋው አስራ ሁለት ኢጲስ ቆጶሳት (ሐዋርያት) መድበው በታላቁ ገዳም ደብረሊባኖስ በአርሞም በተዘግሐ ፳፪ ዓመት ከቆዩ በኋላ ከቁመት ብዛት የተነ ሳ አንድእግራቸው ሊሰበር ችሏል።

ክቡር አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት ያለመከራ ፀጋ እግዚአብሔርን ማግኘትይቻልም የሚለውን የአምላክ ቃል ያውቃሉና እንደገና ሰባት ዓመት በአንድ እግራቸው ቆመው ለሀገር ፥ ለቤ ተ ክርስትያን ፥ለምዕመናንና ለዓለም ፀልየዋል። ጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት እንደ ነበያት መጻየትን ሐዋርያትን እንደ ሐዋርያት ስብከትን ተዕምራትን፥እንደሰማዕታት ገድልን መከራን ፥ እንደ ባህታውያን በአርምሞ በሕርመት በተዘግሖ ቢኖሩም "ኦ አዳም መሬት አንተ ወትገብ ውስተ መሬት "የሚለው ቃል ሁሉንም የሚመለከት በመሆኑ ገድላቸውን ሲፈጽሙ ለስም አጠራሩ ምስጋና የሚገባው አምላካችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ድንግል ማርያምን ቅዱስ ሚካኤልንና ቅዱስ ገብረኤልን እንጦንስና መቃርስቅዱሳን አበውን አስከትሎ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት ፳፱ ዓመት መከራ ወደ ተቀበሉበት ደብረ አስቦ ዋሻ መጣ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባታችን አቡነ ተክለሃይ ማኖትን ሩጫህን ጨርሰሃል ገ ድልህን ፈፅመሐል የድል አክሊል ቀርቦልሃል ከሞት በቀር የቀረህ የለም ስምሕን የጠራ ዝክርህን ያዘከረ መቃብርህን መጥቶ የተሳለመ መጽሐፈ ገድልህን የፃፈ ያፃፈ የሰማ ያሰማ ቤተክርስትያን በስምህ ያሳነፀውን እስከ አስር ትውልድ ድረስ ምሬልአለሁ በማ ለት ቃል ገብቶላቸው ወደ ሰመይ አርጓል።



Created using easyPDF Printer
Click here to purchase a license to remove this image

አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት ከላይ የተጠቀሰውንና ሌላም ቃስኪዳን ተቀብለው ዘጠና ዘጠኝዓመት ከአስር ወር ከአስር ቀን በመኖር ደማቸውን ባፈሰሱበት መከራና ፈተና ባሳለፉበትከጌታ ቃል ኪዳን በተቀበሉበት ደብረሊባኖስ ገዳም ነሐሴ ፳፬ ቀን አርፈዋል።የአባታችን አፅም የፈለሰበትን ግንቦት ፲፪ ቀን በኦታዋ በሚኘው በአቡነ ተክለሃይማኖት ቤተክርስትያን የጌታፍቀድ ሆኖ ከዓመት ዓመት እና ከብራለን።

አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት የተሰጣቸው ቃል ኪዳን ያልጎደለባቸው አሁንም ገደላቸው በሚነበብበት ጽላታቸው በተቀረጸበት ተኣምራትን ያደርጋል ። ይልቁንም ገድላቸውን በፈጸሙበት በታላቁ ገዳም በደብረሊባኖስ ድውያን ይፈወሳሉ ፤ አጋንንት ይወጣሉ ፤የተራቡ ይጠግባሉ ፤ከስምንት ሺ ያላነሱ አባቶች እናቶችና የነገዋ የቤተክርስትያን ተረካቢ ደቀመዛሙርት የአብነት ትምህርት ይማሩበታል።

ይህ ተዓምራት እስከምጽአተ ክርስቶስ ይቀጥላል።
የፃድቁ አባታችን የአቡነ ተክለሃይማኖት ረዲኤትና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን!!!

## ክርስትና

* ጊዜ የሚገድበው፣ቦታ የሚወስነው ሳይሆን፤ ሁልጊዜ የምንኖረው ሕይወት ነው። (ማቴ ፰፣፲፫)
* ፈተናን ፈርተው የሚሸሹበት ሳይሆን ፤በፈተና ውስጥ አልፈው ለክብር የሚበቁበት ሕይወት ነው። (ያ ዕ ፩፣፲፪)
* ለራስ የሚሹትን መልካም ነገር ሁሉ ፤ለባልንጀራ በማድራግ የምንኖረው ሕይወት ነው ። (ማቴ ፯፣፲፪)
* በመንፈስ የሰውነት ሥራ በመግደል፣ፈቃደ ሥጋን ከፈቃደ ነፍስ ለማስገዛት፣የምንኖረው ሕይወት ነው። (ሮሜ ፰፣፲ ፪-፲፬)
* በኋላ ያለውን እየረሳን ፤ በፊት ያለውን በመያዝ፤ለትሩፋት፣ለጽድቅ ሥራ የምንተጋበት ሕይወት ነው ። (ፊሊ ፫፣፲፫)
* ሰው በጥፋት ዘመን ፤ሰው ሆኖ መገኘት ነው። (ኢሳ ፪፣፳-፴)
* በትህትና (ራስን ዝቅ በማድረግ) የምንኖረው ሕይወት ነው። (፩ ጴጥ ፭፣፭-፮)
* የሥጋ ፍላጎታችንን የምንገታበት፤የማንነታችን መታወቅያ ምልክት ነው። (ዘፍ ፴፬፣፲)
* በባህርይ ደካማነት የሚሳሳተውን ሰው፤በመምክርና በመገሰጽ፣ለዛም ሰው በመጸለይ የምንኖረው ሕይወት ነው። (ሮሜ ፲፬፣፩)
* ምንም ተስፋ በሌለበት ሰዓት ፤ተስፋ የምናደርገው ሕይወት ነው። (ዳን ፫፣፲፯)
* ነጻነት ሕይወት ነው። (ገላ ፭፣፲፩)
* የገድል ሕይወት ነው።(፩ኛ ጢሞ ፬፣፯)
* በችግርና በመከራ ጊዜ እግዚአብሔርን በመስገን የምናገኘው ሰላም ነው። (ኢዮ ፩፣፳፩)
* በስሜታዊነት ወይም በአንድ ጊዜ ፍጹምነት ማእረግ የምንደርስበት ሳይሆን፤ በመንፈሳዊ ሕይወት፤ ደረጃ በደረጃ በማደግ የምንኖረው ሕይወት ነው። (ሐዋ ፲፬፣፳፪)
* ጀመረን የምንተወው ሳይሆን፤እስከ ሞት ድረስ ታምነን እንደ ቸርነቱ አክሊል የምንቀበልበት (መንግስቱን የምንወርስበት)ሕይወት ነው። (ራዕ ፪፣፲)
* ውስጣዊ ሕይወትን መቀየር እንጂ ፤በመምሰል ወይም ውጭ ክፍልን ብቻ በማሳመር የምንኖረው ሕይወት አይደለም።(ገላ ፭፣፳፩) ወ.ዘ.ተ.

በመሆኑ በእኛ የክርስትና ህይወት ውስጥ እነዚህ ነገሮች ይታያሉን? ካልታዩ በእግዚአብሔር ቃል መስተዋትነት እራሳችንን እናዘጋጅ። በክርስትና ህይወት አለን የምንል በቅድምያ የቀደሙ አባቶቻችንን መንፈሳዊ ጉዞ መመልከት ይኖርብናል። ምክንያቱም የክርስትና ህይወት ጀማሪዎች ወይም መንገድ ከፋቾች እኛ ባለመሆናችን ፤የግድ ከነሱ ህይወት ብዙ መማር ይገባናል። ቅዱስ ጳውሎስ " የኑራአቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነት ምሰሏቸው። "(ዕብ ፲፫፣፯)ያለውን አብነት ይዘን የቅዱሳን አባቶቻችን የክርስትና ህይወታቸውን በመመልከት ክርስትናን በስም ሳይሆን በተግባር እንድንኖርበት ልዑል እግዚአብሔር ይርዳን።

ምንጭ፤ ቃለ ተዋህዶ ቁ.1 /94



Created using easyPDF Printer
Click here to purchase a license to remove this image